# ቁጩት

ከተዘራ አሰጉ / ከምድረ እንግሊዝ/

ታሪክ ወደ ኋላ ሲዳሰስ
የኛነታችን መቸት ሲናኝ ፤

ህልማችን በይሉኝታ ተለጉሞ
ተጠላልፎ ተመሰጥሮ ተቋጥሮ ፤

ለዓመታት ታልሞ ታቅዶ
ፍቹ ተጣሞ ተፈቶ ፤

የማይደፈረውን ሲሉ አትሞክሩ
ጂምር ውጥናችን ሲያስፎሩሹ ፤

አዚሙ ደንቃራው ትብትቡ
በመካከላችን ተርጭቶ ምታቱ ፤

ፋት እንዳንል ውሃችን
ረሃብ ድህነት ታውጆብን ፤

እጃችን በነጠላ አጣፍተን
በደቦ እንዳንጓዝ ታስረን ፤

ዘለቅን ከዘመነ ዘመናት
ሳንቋደስ ከፀጋው በረከት ፤

እርስ በርስ ሲያላትሙን
በነገር ሸርበው ሲያናቁሩን ፤

እታች ሆነው ሲመጡን
ትተውልን አሰር ሰፈፉን ፤

ባለፈ ታሪክ ተወድረን
በማንነት ጥላ ተጋርደን ፤

ላም አለኝ በሰማይ እንዲሉ
አልቦ ጎተራውን መጨሩ ፤

የሚታይ የሚዳሰሰው በረከቱ
ምዕናብ ግዑዝ ሆኖ መመለኩ ፤

የሚበላ የሚጠጣው ከጓሮ
ዕርማችሁ ነው ተው ተብሎ ፤

በሃብት መክሊታችን ፈረዱ
በመቁንን ሊቸሩን ዳዱ ፤

ዳግም ሊያደናግሩን ዳዱ
ያቅኙዎቻቸውን ዱለታ ሊቀኙ

ሴራ ዱለታውን እያወቁ
ያዛዣቸው ቁልፍ ያዥ ሆኑ ፤

ሃገሬ የደግነትሽ ምላሽ
ሆነ እጂሽ አመድ አፋሽ ፤

የንስር አሞራ ድፍረቱ
አፍሶ ዓሣን ከብሃሩ ፤

በክንፉ ባህሩን ያምሳል
ረስቶ ቸርነት ውለታን ፤

የጠገበ ሲተፋ ማደሩ
እንዲሉ ሆነና ትንግርቱ ፤

ዘመነ ጊዜው ተለውጠ
ቁጭት ብርሃንን ሽቶ ፤

አፈፍ ሲል ሲዳዳ
መሪው አቀናጅቶ ሊነዳ ፤

ያዙኝ ልቀቁኝ ማለቱ
የማያውቁበትን ማጓረሩ መፎከሩ ፤

አባይ ያጋመደው ህዝብ
በቀረርቶ ናዳ አይሸበር ፤

የመለያየት ድር ማጉ
ተበጣጥሷል በአንድነቱ ፤

በጋራ ለጋራ መኖሩ
ሁንዋል የትውልድ ትብዕሉ ፤

እንግዲህ ስማ ወገን
የጨለምተኞችን ላንቃ ስበር ፤

በብርሃን እንዲታጀብ ኑሮህ
ህዳሴህን ናኝ አብስር ፤

መናቆር መጎሻሸምን ሸርሽር
ሃብት ፀጋህን አቁር ፤

ሰላም ልማት ፈንድቃ
በብርሃን ታጅባ ፈክታ ፤

ህልምህ እንዲሰምር አርይ
የዘራህው ማጨጃ ዘመን ፤

እየታየ ነውና አሽቶ
በየ ጓዳህ አገምግሞ ፤

በቁጭት እንደኖሩ ማሸለብ
ይብቃ  ከእንግዲህ ወገን ፤

አባይ ፊቱ ዞር ሲል ወደኛ
የኛም ቀልብ ይመለስ ይቅና ፤

ግቤ ተከዜ በለስ
የሕዝባዊነት ምልክት ፤

የብሔር ብሔረሰቦች ሁደት
በአንድነት መትመም ተምሳሎት ፤

የቻልነውን የአቅማችን ለግሰን
ወገንን ሃገርን ጠቅመን ፤

የነገን ተስፋ መሰነቁ
ይህ ነው የኢትዮጵያዊነት ውሉ፤

ሃገረ ኢትዮጵያ አንሰራርታ
ማየቱ በህዳሴው ተውባ ፤

ይህ ነው የቁጭት መወጫው
የድህነት የኋላቀርነት መስበሪያው ፤

የኢትዮጵያዊነት ማገሩ ጣራው
አሸራ መሰረቱ የአንድነት ዳፋው ፤

ጂምሩ ከአፋፍ ደርሶ
አዲስ ታሪክ ተመዝግቦ፤

እናያለን ኃይላችን ተመንድጎ
ድህነት መቀመቅ ገብቶ ።

ከተዘራ አሰጉ / ከምድረ እንግሊዝ/